ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በሰኔ 14 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ከጫጉላው ወራት በኋላ !

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያካሂደው ቆራጥ ትግል ምክንያት፤ ወያኔ፤ የሥልጣን ሽግሽግ ለማድረግ ከመገደዱ የተነሳ፤ የአዲስ ጠቅላይ ምኒስትር መምጣት ተከሰተ። አዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ምኒስትር ወደ ሥልጣን ከመጣም፤ ይኸውና አንድ መቶ ቀናትን አስቆጥሯል። አንድ መቶ ቀን፤ ለጫጉላ ወራት ጥቂት ነው አይባልም። በነኝኽ ቀናት፤ ወደ ለውጥ ሊያስኬዱ ይችላሉ በሚባሉ በርካታ ንግግሮችን፤ ነገር ግን ሚዛን ደፊዎች ናቸው የማያሰኙ ድርጊቶችን ሲያካሄድ ቆይቷል ። ሀገሪቱም ከፈርዖኖች የጨለማ አገዛዝ እየተላቀቀች ነው በሚያስመስል መልኩ ፤ ማርና ወተት ልታዘንብ ወደምትችለበት የተስፋ ምድር፤ ፈቷን እያዞረች ትገኛለች የሚሉ ዜጎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ይኽንን ቢመኙ አይፈረድባቸውም።

የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ ማርና ወተት ማዝነብ ወደምትችለው፤የተስፋዋ ምድር ወደ ዕውነተኛዋ ኢትዮጵያ የሚያሻግረውን፣ ሙሴን ቢመኝም፤ የራሱን መሪ እስካልመረጠ ድረስና ፤ ወያኔ መንግሥታዊ ሥልጣኑ ጎምጥጦ እስከያዘ ደረስ ፤ ስር ነቀል ለውጥ ቀርቶ፤ የመዋቅር ማሻሻያ እንኳ ይመጣል ብሎ ማሰብ የቀን ኅልም ነው። ሕዝባዊ ትግል፤ ቆራጥነት ብቻ ሳይሆን ፤ የወሳኝነት ባህርይም ያለው መሆኑን የሚገነዘቡ ብልሆች፤ ሠልፋቸውን ከሕዝብ ጋር ያስተካክላሉ። አዲሱ ተሿሚ ብልኅነቱን የሚያረጋግጠው፤ ሠልፉን ማስተካከል ያለበት፤ ከሕዝብ ጎን በመቆም ብቻ ነው ብለው የሚናገሩ ብዙዎች ሆነዋል ።

ከሃያ ሰባት ዐመት ዘመነ- ፍዳ በኋላ ፤ የተስፋ ጭላንጭል እየመጣ ነው ቢባል ፤ የሚያስገርም ሊሆን አይችልም። ድቅድቅ በሆነ ጨለማ ተሸብቦ የቆየ ኅብረተሰብ፤ ከረዥሙ የጨለማ ዋሻ መጨረሻ ትንሽ የብርሃን ፍንጣቂ ማየት ጀምሬአለሁ ብሎ ተስፋን ቢሰንቅ አያስደንቅም። ነገር ግን፤ ሰማይ ምድሩ ለተደፋበት ሕዝብ፤ የነፃነት መኅናፀፊያ ማግኘትን ይፈልጋል ቢባልም፤ ጓጉቶ የጠበቀውን ተስፋ፤ ወደ ተጨባጭ ወጤት እስካልተረጎመለት ድረስ ፤ " የከርሞ ሰው ያድርገን " ብሎ ያኮርፋል እንጅ ፤ በዘወትር ህይወቱ ላይ አንዳችም ለውጥ አያይም ።

አሁን የተከሰተው፤ የነባቢት እንጅ የድርጊት መቋጠሪያ አይደለም። የነባቢት ሙያ ደግሞ፤ በአመዛኙ፤ የአፍዝ-የአደንግዝ ምትሃት ሆኖ ሕዝብን ከማደንዘዝ ያለፈ ፋይዳ አያመጠም። በማያበራ ተስፋ እያቋመጡ መኖር ፤ የአምባገነኖች ሰለባ የሆነ ህዝብ ዕጣ ፈንታ ነው። እኛም ፤ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ክፍል መመደባችን ያስቆጨናል።

ይኽ እንዳለ ሆኖ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄ፤ አሁንም የሥር ዓት ለውጥ እንደሆነ አዲሱ ተሿሚ ፤ ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለበትም። አሁን ዛሬ፤ የሥርዓት ለውጥ፤ በጥቂት ግለሰቦች አቅምና ጉልበት ብቻ እውን ይሆናል ተብሎ በብዙ ሕዝብ ዘንድ የሚጠበቅ አይሆንም ። ህዝብ ፤ ፍራሽ አሳዳሽ ለውጥን አይፈልግም ።

ወያኔዎቹ ለውጥ አጋጆች ናቸው። ለውጥ እንዲመጣ ካለመፈልጋቸው የተነሳ የራሳቸውን ሹም በለመዱት ተንኮላቸው ጠልፈው ሊጥሉት ይችላሉ። ለውጥ አጋጆችን መቋቋም ከፈለገ፤ አዲሱ ሹም የለውጥ ፈላጊዎች አጋር እንዲሆን

ይጠበቅበታል ። ጠቅላይ ምኒስትሩ ሁለት ምርጫዎች እፊቱ ላይ አፍጥጠው ያዩታል ። ለውጥ ፈላጊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል ሲሆን፤ ለውጡን ለማገድና ለማጨናገፍ የቆመው ወያኔ በሌላ ወገን ተሰልፈዋል። በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ወሳኔ ለሚጠናቀቀው ሕዝባዊ ዐመፅ ወገንተኛ መሆኑ፤የታሪክ ሰሪዎች ተልዕኮ እንደሆን መዘንጋት አይኖርበትም።

አዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ምኒስትር ፤ እፊቱ የተደቀነበት ግዳጅ ቀላል እንደማይሆንለት የብዙዎቹ ዕምነት ሆኗል፡፡ ምክንያቱም ለሠላሳ ዐመታት ያኽል በወያኔ ሽኮፍ የተተበተበበትን ተንኮልና አሸንካላ እንዲሁ በቀላሉ ሰባብሮ ለመውጣት ቀላል ተግባር ስለማይሆን ነው ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ በአግባቡ መመለስ መቅደም ይኖርበታል። የ1983 ቱን የወያኔ ስብስብ ከመቃብሩ አስነስቶ በአዲስ ሊያስፍኑ ከሞከሩ ከወዲሁ ሽንፈታቸውና ውድቀታቸው የሚረጋገጥ ሁኔታን ማረጋገጥ ዋስትና የኖረዋል ። ሌንጮም ሆነ ሌሎቹ ወያኔዎችና የወያኔ ሻዕቢያ አሽከሮች ቢኮለኮሉ የታሪክ ምጸት ተደገመ የምንለው እንጂ ለሀገራችን የሚበጅ ሊሆን የሚችል አይደለም ።
ከሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ከሚያጣጥረው ከወያኔ አገዛዝ ይልቅ ፤ ኃያልነቱ፤ በጊዜና በቦታ ሊወሰን ከማይችለው ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚሰለፍ ታሪክ ሰርቶ ያልፋል ። በቅርቡ የተፈራረቁት ሁሉ አስመስጋኝ ታሪክ ሳይሰሩ ነበር የተሰናበቱት ። " መካሪ የሌለው ንጉሥ ፤ ያለ አንድ ዐመት አይነግስ " ሆኖ እንዳይቀር፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ ምክርና ተግሳፅ፤መስማት ፤የሕዝብን ፍላጎት ቅድሚያ ሰጥቶ ማሟላት መሠረታዊ ጥያቄዎቹን ለመመለስ መጣር፤ ፤ የሚፈለገውን ሁሉን አቀፍ ሽግግር እውን ለማድረግ መጣር ሕዝባዊነትን የማስመስከር ጥረትን ያመለክታል ።

ወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ የሚሽከረከረው፤ ገና ዕልባት ባልተገኘበት የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄ ዙሪያ ነው ። መሠረታዊ ጥያቄ ማለት ስር -ነቀል ለውጥ ማለት ነው ። ይኸ ማለት ደግሞ፤ የሥር ዓት ለውጥ ማምጣት ማለት ነው ። ስር ሰድዶ የገነገነውን የዘረኛ ሥርዓት ለመለወጥ ፤ በግድም ሆነ በውድ፤ የኃይል ሚዛኑን ወደ ህዝብ ሊያጋድል የሚችልበትን ተግባር በቅድሚያ ማስቀደም ይገባል ። የወያኔን አገዛዝ ለመለወጥ፤ መጀመሪያ መዋቅሮቹ ተንገጫግጨው እንዲወላልቁ ማድረግ አስፈላጊ ነው ። አዲስ ሹም ሲፈተሽ፤ ይህን ከማድረግ አንጻር--ከንግግር ባሻገር-እምብዛም ሲንቀሳቀስ አይታይም። ያደርጋል ተብሎም አይጠበቅም። ምክንያቱም አሁንም ቢሆን፤ የኃይል ሚዛኑ፤ በወያኔ መዳፍ ስር በመሆኑ ነው።

አዲሱን ሹም እንደ ልቡ እንዲንቀሳቀስ ከማያስችሉት ዋና ዋና ዕንቅፋቶች ፤ ለሃያ ዐመታት ሲያገለግለው የነበረው የመንግሥት ተቋማትና የመጨቆኛ መሳሪያዎቹ ናቸው። ያም ቢሆን ቅሉ፤ በግንባር ቀደም ከተሰለፉት አንድ አንድ የሥርዓቱ ተቋማት መሪዎቹ መካከል ለውጥ አላደረገም አይባልም ። አድርጓል። የሰዎች መለዋወጥ ማለት ግን የተቋማትንና የመዋቅር ለውጦች አድርጓል ማለት አይደለም ። የወያኔ ስለላ ድርጅት አራጊ ፈጣሪ በመሆን ፤ከፍተኛ ወንጀል የፈፀመውን የሀገርና የሕዝብ ጠላት፤ ጌታቸው አሰፋና የወያኔን ጦር ኤታ ማዦር ሹም፤ ሣሞራ ዮኒስ ተነስተዋል የተባለ ቢሆንም፤ ተቋማቱና መዋቅሮቻቸው ግን፤ ፍንክች-ንቅንቅ አልተደረጉም። እንዲያውም በአዲስ ዘዴ እየተዋቀሩ ነባርና አክራሪ የትግራይ ብሄረተኞች ተሹመውባቸዋል ። ከወያኔ ጥብቅ መዳፍ ቁጥጥርም አለመውጣታቸው ገሃድ

ነው። ሦስቱ ዋና ዋናዎች ናቸው የሚባሉት ፤ ዐደገኛ የመጨቆኛ መሳሪያዎች አሁንም ከወያኔ ጥብቅ ቁጥጥር ነፃ አልሆኑም ።

እነርሱም፡--- 1ኛ. የጦር ኃይሉ **2ኛ.** የመረጃው ክፍል 3ኛ. ፍርድ ቤቶች፤ ወህኒ ቤቶችና የፖሊሱ ኃይሉ ፤ በወያኔ ማዕከላዊ ዕዝ- ቁጥጥርና ስምሪት ስር ናቸው ። ተቋማቱ ፤ ከነ መዋቅራቸው ሳይሸራረፉ፤ አሁንም በወያኔ ጥብቅ ቁጥጥር ስር በመሆናቸው፤ አዲሱን ሹም ቀስፈው ይዘውታል ። አሁን ተጨባጩ ሁኔታ እንደሚያመለክተው ፤ የሀገሪቱን ሙሉ መንግሥታዊ ሥልጣንን ይዞ የሚመራትና በኃላፊነትስ የሚጠየቅ አካል የት ላይ እንደሆነና መንግሥት ተብሎ የሚጠራውንም ይህን ተቋም ማን እንደሚቆጣጠረው ፤ እንደሚያዝዘው፤ እንደሚዘውረውና ፤ ብሎም ትዕዛዙንስ ማን እንደሚያስፈፅመውና እንደሚከታተለው ግልፅ ያልሆነ ቢመስልም፤ የወያኔ ሥርዓት በተጨባጭ እየተናደ ነው ብሎ መደምደሙ በጣም ስህተት ይሆናል ። በርግጥም የሚወጡት መግለጫዎች የተለያዩ መሆናቸው ብቻ ሳይሆኑ ፤ አንደኛው ሌላኛውን የሚፃረሩና የሚያወናብዱ ናቸው። ሁሉም በየበኩሉ ፤ ዐውራ ዶሮ ሆኖ ለመውጣት ይፍጨረጨራል ። እርስ በእርስ ይጠባበቃል ። ተፈራርቶ እንደ ጠላት ይተያያል ፤ ይሸቀዳደማል ። ይጠላለፋል ። ባለፈው ወር የተከናወነው ድራማ ፤ በቂ ገላጭ ሆኖ አልፏል። እርሱም፤ የአልጀርሱን ወሳኔ በመቀበል ባድመንና ዛላአንበሳን ለኤርትራ መልቀቅን አስመልክቶ የወጣው መግለጫ ሕዝባዊ ተቃውሞ ስለገጠመው፤ ወያኔዎቹ፤ አዲሱን ሹማቸውን ከድተው ያወጡት ተፃራሪ መግለጫ ነው ።እርሱን ገፋፍተው ያን ወሳኔ እንዲናገር ከአደረጉ በኋላ ፤ውሳኔው የሕዝብ ተቃውሞ ሲገጥመው፤ ወያኔዎቹ፤ ከድተው ሕዝበኞች ለመሆን ሞከሩ ። በዚህ ወንጀላም አዲሱን ሹም ጉድኋድ ሊቆፍሩለት ይዘጋጃሉ። ይህን በተምለከተ በቂ መረጃም አለ ።ወያኔ ይኸንን ማድረግ ደግሞ፤ የግል ባኅሪው ሆኖ ቆይቷል ።

የወያኔ ቀንደኞች ፤ በመካሄድ ላይ ያለውን ሂደት አልወደዱትም። ከታላቅ ስጋት ላይ እንደ ወደቁ በድብቅና በግል በሚያደርጓቸው ስብሰባቸው ይናገሩታል ። ጥቅማችን ተነካ ፤ ክብራችን ተደፈረ ፤ እየተገፋን ወደ ዳር እየወጣን ነው። የበላይነታችን አደጋ ላይ ወድቋል። ሁሉም አድሞብናል ። የትግራይን ሕዝብ ሁሉም ተጻርሮ ቆሞበታል ። ወዘተ ወዘተ ከሚል ድምዳሜ እየደረሱ፤ አሁንም እንደገና የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ለማጋጨት ተንኮላቸውን በመሸረብ ላይ ይገኛሉ። ለሌላ ዙር አውዳሚ ዕልቂት እንዲዘጋጅ እየገፋፉት ነው። የዚኽ መሰሪና መርዘኛ አድማ ግንባር-ቀደም ጠንሳሾች **፤ዐባይ ፀሀይ ስዩም መስፍን ፤ ኅላዊ ዮሴፍ ፤ ስበኀት ነጋ ፤ በረከት ስምኦን፤** በአንደኛ ደረጃ ተጠቃሾች ናቸው። ዞሮ ዞሮ፤ የሀብት ንብረት ጉዳይ በመሆኑ ፤ የዘረፉት ሀብት እንዳይነጠቅባቸው ያካበቱት ንብረት እንዳይወረስባቸው፤ ያሸሹት የሀገር ሀብት እንዳይመረመርባቸው እስከ መጨረሻ እስትንፋሳቸው ድረስ ይሟሟታሉ። ይፈራገጣሉ። ከኢትዮጵያ የወርቅ ማዕድን፤ እንዲህ በቀላሉ አይለቁም ። እንዲሁ በሠላም አይሄዱም ። በሕዝብ ዐመፅ ካልሆነ በስተቀር!

በኢሕአዴግ ስር የተጠጉት ሌሎቹ ሦስት ሀረግ ሬሳ ድርቶች ፤አሁንም ከህወሃት/ ወያኔ ጥብቅ ቁጥጥር ነፃ አልወጡም ። የየራሳቸውን የግል ነፃነት ማስከበር ባለመቻላቸው ፤ ወክለነዋል የሚሉትን የኅብረተሰብ ክፍል ነፃነት ማስከበር ቀርቶ፤ የትና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ እንኳ፤ ማወቅ አይችሉም። አሁን የወያኔ ኮለኔል በመሾሙ ሳቢያ በተፈጠረው የኢሕአዴግ ምስቅልቅል ምክንያት፤ ብዙ ያልተጠበቁ ክስተቶች ተስተውለዋል። የክስተቶቹ

መፈጠር ዋነኛው ምክንያት፤ የሕዝቡ ዐመፅ ያስከተለው ሀገራዊ ነውጥና በወያኔ ላይ የፈጠረው መደናገጥ ነው ። የወያኔ መደናገጥ ፤ በተለጣፊ አባል ድርጅሮች ዘንድ ፤ በአንድ በኩል፤ ብዥታን፤ የመቁነጥነጥንና ግራ የመጋባትን ሁኔታ ሲፈጥርባቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዕፎይታን፤ መረጋጋትን፤ ከወደቀባቸው ተፅዕኖ ነፃ ለመውጣት የመፈራገጥን ስሜትን ሳይፈጥርላቸው አልቀረም ። ጥቅመኛውና ዕበላ-ባዩ ብርክ ይዞታል። ሚናውን ለመለየት ተቸግሯል። " የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል " በመሆኑ፤ የተዘረፈ የሕዝብ ሃብት ያካበተው ሁሉ፤ " አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት " ከሚል ደረጃ በመድረሱ፤ የሕዝቡን አቸናፊ ሆኖ መውጣት ይጠባበቃል። መርኅና ይሉኝታ የሚባል ነገር ስለማያውቅ፤ የማታ ማታ ሰልፉን እንደሚያሳምር ምንም ጥርጥር አይኖርም።

አሁንም የወያኔ አገዛዝ ከድንጋጤና ከመርበተበት ያለፈ ስጋት አላጋጠመውም። ይህ ስለተባለ ደግሞ፤ ወያኔዎቹ እንደ ቀድሟቸው የልብ ልብ እየተሰማቸው መግዛታቸውን ቀጥለዋል ማለት አይደለም። እንደ በፊቱ፤ ገላቸውን ሰድደውና ተኩራርተው መግዛት አልሆነላቸውም። ይኽ ማለት ግን እንደ ድሯቸው ሀገር የማጥፋትና ሕዝብ የመበደል ቁመናቸው ሙሉ በሙሉ ተዳክሟል የሚለውን እንዝኅላልነት ማስተናገድ አያስፈልግም። አሁን ወያኔ፤ በማጥቃት ደረጃ ሳይሆን፤ በከፊልም ቢሆን በመከላከል ደረጃ ላይ እንደሆኑ ፤ እርሱም ሊክደው አይቻልም ። ያለማቋረጥ የሚያደርጉት ምሥጥራዊ ስብሰባቸው፤ በቁጭትና ፍርሃት ፤ በስጋትና በንዴት፤ ተሰፋ በመቁረጥና የቆሰለ ዐውሬ በሚያሰቃየው ኅመም የተሞሉ እንደሆኑ፤ አፈትለከው ከሚወጡ መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል።

የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ወዴት እንደሚያመራ በቅርብ የመከታተሉ ተግባር፤ ይንን አፋኝ አገዝዝ ተጻርሮ የቆመው ኃይል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ጠቅላይ ምኒስትሩ፤ በጫጉላ ወራት ማከናውን ከነበራበት ሁኔታ ተሻግሮ፤ ስትራተጂያዊና ዘላቂ በሆኑ ተግባራት ማተኮር ይጠበቅበታል ።

**1ኛ.** ለሥርዓት ለውጥ ወደ ሚያሸጋግሩ ሂደቶች ላይ ማተኩር መላው ሕዝብ አስፍስፎ የሚጠብቀው ፍላጎት ነው።

**2ኛ.** ሁሉንም ድርጅቶች ሊያሳትፍ የሚችል ሀገራዊ ጉባዔ መጥራት የቅድሚያ አጀንዳ ሊሆን ግድ ነው።

**3ኛ.** ይህንን ለማሳካት፤ የዴሞክራሲ መብቶች መስፈን ወሳኝ እንደሆነ ተረድቶ፤ ግብዐቶችን ማመቻቸት ወሳኝ ነው ። ሠላምና ዕርቅ ለማምጣት የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎን ይጣይቃል ። አሳታፊ ዴሞክራሲ ዕውን ሊሆን የሚችለው፤ የሕዝቡን ሙሉ ተሳትፎና ይሁንታን ሲያገኝ ብቻ ነው።

**4ኛ.** ከአንድ እስከ ሦስት ተራ ቁጥሮች የተመዘገቡትን መፈፀም፤ ወቅታዊ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ የሚያስገድደው ጉዳይ ነው ።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ።

ጸረ ወያኔ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !